31ኛ ዓመት ቁጥር

202 አሶሳ፣

የካቲት/ 2017 ዓ.ም

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት

## ልሳነ-ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 293

ያንዱ ዋጋ----------

## LISAN-HIG GAZETA

Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State፣

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ፣**

### አዋጅ ቁጥር 202/2017 ዓ.ም፣

### የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ መንግሥት /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 31/1995 እንደገና ለማሻሻል የወጣ የክልል ምክር ቤት (ማሻሻያ) አዋጅ)፤

የክልሉ ባለቤት ብሄረሰቦች ስያሜ የብሄረሰቡን ታሪክ፤ ማንነት፤ ባህል እና ወግ የሚያመላክት መሆን ያለበት በመሆኑና በዚህ ረገድ የታዩ ስህተቶችን ማስተካከል በማስፈለጉ፤

እያደገ በመጣዉ የራስ አስተዳደር ጥያቄ መነሻነት በአዲስ በተደራጁና፤ ሊደራጁ በሚችሉ የከተማ አስተዳደር፤የወረዳና የልዩ ወረዳ ፍትሃዊ ዉክልና ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ መንግሥት /እ□ተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 31/1995 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የክልሉ ምክር ቤት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አዉጥቷል፡፡

## አንቀጽ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ **"የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ መንግሥት/እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 31/1995 እንደገና ለማሻሻል የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 202/2017 ዓ.ም** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2

## የህገ-መንግስት ማሻሻያ

ሀ. በህገ መንግስቱ መግቢያ /preamble/ አራተኛ ፓራግራፍ ላይ እኛ የበርታ፣ እያለ በሚጀምረዉ የብሄረሰቦች ዝርዝር ዉስጥ፤-

እኛ የበርታ፣ የሚለዉ ስያሜ ተሰርዞ "እኛ የቤኒሻንጉል፣ ……" በማለት እንዲጀምር ተደርጓል፡፡

ለ. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 2 በብሄረሰቦች ዝርዝር ዉስጥ በርታ የሚለዉ የብሄረሰብ ስያሜ ተሰርዞ "የቤኒሻንጉል……፣ በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

ሐ. በህገ መንግስቱ ስለ ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ በሚደነግገዉ አንቀጽ አራት ስር በንዑስ አንቀጽ ሁለት "የክልሉ ዓርማ ዙሪያ በቀርቀሃ የተከበበ ሆኖ በመሃሉ ወርቅ የያዘ ገበታ እና የማሽን ጥርስ ያለዉ ይሆናል" ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል በሚል የተደነገገዉ ተሰርዞ፤

አንቀጽ 4 (2) …."የክልሉ ዓርማ መደቡ አረንጓዴ የሆነ ክብ ሆኖ በዉስጡ ሰማያዊ ቀለም፤ቀርቀሃ፤ የክልሉ ካርታና በካርታ ዉስጥ ያለ ወርቃማ ቀለም፤ ከካርታዉ አናት ላይ ያረፈ ግድብ፤ እንዲሁም አምስት ኮኮቦች እና የማሽን ጥርስ የያዘ ይሆናል" ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡ በሚል ተስተካክሏል፡፡

መ. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 48 አንቀጽ 2 ስር "የምክር ቤት አባላት በምርጫ ክልለ ዉስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ስርዓት ይመረጣሉ፡፡ የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የህዝብ ብዛትን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡ የማኦና ኮሞ ብሄረሰቦች ዉክልና በልዩ ሁኔታ ይታያል፡፡ ጠቅላላ የምክር ቤት አባላት ቁጥር ከአንድ መቶ አይበልጥም፡፡ የተለየ ዉክልና እንደሚያስፈልጋቸዉ የታመነባቸዉ ህዝቦች በምርጫ ምክር ቤቱ ዉስጥ

ይወከላሉ፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል” በሚል ከተደነገገዉ ዉስጥ “ጠቅላላ የምክር ቤት አባላት ቁጥር ከአንድ መቶ አይበልጥም” የሚለዉ አገላለጽ ብቻ ተሰርዞ፡-

በአንቀጽ 48 ስር አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተጨምሮ፡-

አንቀጽ 48 (3) “ጠቅላላ የምክር ቤት አባላት ቁጥር ከ165 መብለጥ የለበትም” በሚል ተሻሽሏል፡፡

መ. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 48 ስር ቀደም ሲል የነበሩ የንዑስ አንቀጽ 3፣4፣5፣6 እና 7 ድንጋጌዎች እንደ ቅደም ተከተላቸዉ ተሸጋሽገዉ በአንቀጽ 48 ስር ንዑስ አንቀጽ 4፣5፣6፣7 እና 8 ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 3

## አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከጸደቀበት ከየካቲት 11 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ፣ የካቲት 11ቀን 2017 ዓ.ም

አሻደሊ ሐሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት